# 2. በቅንጅቱ ውስጥ በተነሱ አከራካሪ ጉዳዮች (Issues) የማን አቋም ትክክል ነበር?

በቅንጅቱ የትግል ሂደት ውስጥ ከተከሰቱ በርካታ አከራካሪ ጉዳዮች መካከል ቢያንስ ስድስቱ በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡ እነሱም - በኢንጂነር ኃይሉ ሻዎል የመሪነት ጥያቄ፣ በምርጫው ቅንጅቱ የሚያገኘው ከፍተኛ ውጤት ምን ሊሆን ይችላል? በሚለው ቅድመ-ግምት፣ የምርጫ ችግሮችን በማጣራቱ ሂደት፣ በጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት ምሥረታ ጥያቄ፣ ፓርላማ በመግባትና ባለመገባት ውሳኔና በቅንጅቱ የውህደት ጥያቄ ዙሪያ የተነሱ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ በእነዚህ አከራካሪ ጉዳዮች ሁሉ እሳቸው የተከተሉት አቋም ትክክል እንደነበር በመፅሐፋቸው ውስጥ በሰፊው አትተዋል፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ያራመዱት አቋም ምን ያህል ትክክል እንደሆነ እስኪ እያንዳንዱን አከራካሪ ጉዳይ በተናጠል እያነሳን ለማየት እንሞክር፡፡ በቅድሚያ ግን አንባቢ እንዲረዳልኝ የምፈልገው አንድ ቁም ነገር ከላይ በዝርዝር ከተጠቀሱት ስድስት አከራካሪ ጉዳዮች መካከል የምርጫ ውጤቱን የማጣራት ሂደትን ከሚመለከተው ጉዳይ በስተቀር በቀሪዎቹ አምስት ጉዳዮች ላይ እኔ በቅንጅቱ ውስጥ ያራመድኳቸውን አቋሞች በሙሉ በኢዴአፓ-መድህን በኩል እንደ ድርጅት አስቀድመው ተወስነው የተሰጡኝ እንጂ ዶ/ር በርሃኑ እንደፃፉት እኔ በግሌ ያራመድኳቸው አቋሞች አለመሆናቸውን ነው፡፡

## 2.1. የኢንጂነር ኃይሉ ሻዎል የመሪነት ጥያቄ

በቅንጅቱ ምስረታ ወቅት የቅንጅቱ መሪ የሚሆን ሰው ሲመረጥ ቢያንስ የሚከተሉት ሦስት መስፈርቶች ግምት ውስጥ እንዲገቡ ኢዴአፓ-መድህን ሃሣብ አቅርቦ ነበር፡፡ 1ኛ. ቀደም ሲል በኢዴአፓ-መድህንና በመኢአድ መካከል የነበረው አለመግባባትና መናቆር በአዲሱ ቅንጅት ውስጥም ተከስቶ ችግር እንዳያስከትል የቅንጅቱ መሪ የሚሆነው ሰው ከሁለቱ ድርጅቶች ውጭ እንዲሆን፣ 2ኛ. በወቅቱ ሊቋቋም በዝግጅት ላይ የነበረውን ቅንጅት "የቀኝ ኃይሎች ስብስብ" በሚል ፍረጃ ገዥው ፓርቲና አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች "የነፍጠኛ አማራዎች" ስብስብ አድርጎ የማጥላላት ዘመቻ ጀምረው ስለነበረና ይህም አይነቱ ዘመቻ ቅንጅቱ በተለይም በኦሮሚያና በደቡብ ክልል አካባቢ የሚኖረውን የወደፊት ተቀባይነት ችግር ውስጥ የሚጥል ስለሆነ ቢቻል የቅጅቱ መሪ የሚሆነው ሰው የአማራ ተወላጅ እንዳይሆን ቢደረግ የተሻለ ስልት እንደሚሆን 3ኛ. የቅንጅቱ መሪ የሚሆነው ሰው የተሻለ የመሪነትና ተናግሮ የማሳመን ብቃት ያለው ሰው መሆን አለበት የሚሉ ነበሩ፡፡ በእነዚህ ሦስት መመዘኛዎች መሠረት ኢንጂነር ኃይሉ ሻዎል ለቅንጅቱ መሪነት የሚመጥኑ ሰው ናቸው ብሎ ስላላመነ ኢዴአፓ-መድህን የእሳቸውን በመሪነት መመረጥ ተቃውሞ- በአንፃሩ ዶ/ር ብርሃኑ የቅንጅቱ መሪ ቢሆኑ ሦስቱንም መመዘኛዎች በማሟላት ረገድ የተሻሉ ይሆናሉ የሚል ሃሣብ አቅርቦ ነበር፡፡

ዶ/ር ብርሃኑ በመፅሐፋቸው ይህንን የኢዴአፓ-መድህን አቋም በሁለት ምክኒያቶች እንደሚቃወሙ ገልፀዋል፡፡ አንደኛው ምክኒያት ህብረ-ብሔራዊ በሆነው ቅንጅት ውስጥ መሪው ከእከሌ ብሔረሰብ ይሁን - አይሁን ብሎ ሃሣብ ማቅረብ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን - ሁለተኛው ምክኒያት ኢንጂነር ኃይሉ ለቅንጅቱ መሪነት ብቁ ሰው ናቸው የሚል ነው፡፡ የመጀመሪያውን የዶ/ር ብርሃኑን መከራከሪያ ነጥብ ትክክለኛ አስተሳሰብ ነው ብሎ መውሰድ ያስቸግራል፡፡ ከአገራችን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ አንፃር የድርጅት መሪዎችን ብሔረሰብዓዊ ተዋፅኦ ግምት ውስጥ ማስገባት በምንም መመዘኛ ጠቃሚ እንጂ ጐጂ አይሆንም፡፡ በእኔ እምነት ማንኛውም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውጤት አመጣለሁ ብሎ የሚንቀሳቀስ ህብረ ብሔራዊ ድርጅት ይህንን እውነታ ግምት ውስጥ ካላስገባና የተለያዩ ብሔረሰቦችንና የኃይማኖት ተከታዮችን ተሳትፎ በሚገባ በፓርቲው ውስጥ ማሳየት ካልቻለ በስተቀር ውጤታማ ይሆናል ብዬ ለመገመት ያስቸግረኛል፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን

አባባላቸውን ትክክለኛ የራሳቸው አቋም አድርገው እስከመጨረሻው ቢያራምዱት ብዙም ባልከፋ ነበር፡፡ ነገር ግን ዶ/ር ብርሃኑ በሌላኛው የመጽሐፋቸው ክፍል ውስጥ ቅንጅቱን ለማዋሃድ በታሰበበት ወቅት የቀስተዳመናም ሆነ የቅንጅቱ ዋና አመራሮች ምን ያህል ብሔረሰብዓዊ ተዋፅኦን እንዲጠበቁ ለማድረግ እሳቸው እንደጣሩ ገልፀዋል፡፡ ይህንን እርስ በርሱ የሚጋጭ የዶ/ር ብርሃኑን አቋም ስናይ ዶ/ር ብርሃኑ መጀመሪያውኑም የኢዴአፓ-መድህንን አቋም ለመቃወም ሲሉ እንጂ ጉዳዩን ከልባቸው  እንዳላመኑበት የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ -ኢንጂነር ኃይሉ ሻዎልን ቅንጅቱን ለመምራት የሚያስችል ብቃት እንዳላቸው ሰው አድርገው የገለፁትም ሃሣብ ምን ያህል ትክክል እንዳልነበር ሌላ መረጃ መጥቀስ ሳያስፈልግ እራሳቸው ዶ/ር ብርሃኑ ስለ ኢንጂነር ኃይሉ የአመራር ብቃት ማነስ በመፅሐፋቸው ውስጥ የገለፁትን ማየት በቂ ይመስለኛል፡፡

"…. ኢንጂነር ኃይሉ አንዳንድ ጊዜ ሊቀመንበርነቱን ይረሳና ክርክሩ ውስጥ ገብቶ ብዙ ሰዓት ይወስዳል፡፡ ይህ ሲሆን 'ይህንን አትችልም፣ ለራስህ ብዙ ጊዜ እየሰጠህ ነው፣ በትክክል ስብሰባውን ምራ' እየተባለ ተግሳጽ ይቀርብበታል፡፡ ብዙውን ጊዜ ወዲያውኑ ይታረማል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የበለጠ ንዴት ውስጥ ሲገባም 'ተናደደ' ብሎ የሚተወው አልነበረም፡፡ አንድ ቀን ትዝ ይለኛል በጣም የተሟሟቀ ክርክር እየተካሄደና አቶ ኃይሉ የክርክሩ ዋና ተዋናኝ ስለሆነ፣ የሊቀመንበርነቱን ስራ ረስቶት ብዙ ሰዎች እጃቸውን ቢያወጡም በደንብ አይመለከትም ነበር፡፡ ከዚያም በባሰ ለአንድ ሰው እድል ሰጥቶ ያ ሰው የተናገረው እሱ ካለው ጋር የሚፃረር ከሆነ እሱ ሲጨርስ ወዲያውኑ ለተነሳው ሃሣብ መልስ ራሱ ይሰጥና ይህን ሲያብራራ ብዙ ጊዜ ይወስዳል፡፡ በዚህ ጊዜ የተወሰኑ ሰዎች በጣም በመበሳጨት የሥነ-ሥርዓት ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ….. አቶ ኃይሉም በዚህ ተበሳጭቶ ይዞት የነበረውን የእጅ ቦርሳ ዘጋግቶ 'እንዲያውም ሊቀመንበርነቱን ትቼላችኋለሁ' ብሎ ተነስቶ ሊወጣ ሲል እዚያ የነበረው ሰው ሁሉ (የእሱን ሃሣብ የሚደግፉትም ጭምር) ተቆጥተው የተነሳው ሃሣብ ልክ እንደሆነ፣ ከሁለቱ ሚናዎች መምረጥ እንዳለበትና ስብሰባውን በትክክል መምራት እንደሚገባ ነግረውት፣ እሱም ብስጭቱ ጋብ ሲልለት ስህተቱን ተቀብሎ ውይይቱን መምራት ቀጠለ፡፡  ….አቶ ኃይሉ አንዳንድ ጊዜ በቃለ-መጠይቅ ወይንም በአጋጣሚ በጭንቅላቱ ውስጥ ያለን ነገር ገና ቅንጅቱ አቋም ሳይወስድበት ይናገራል፡፡ ይህንን ሲያደርግ አንዳንዴ የግሌ አቋም ነው ይላል፤ አንዳንዴ ምንም አይልም፡፡" (ገፅ 368)

"…. እንጂነር ኃይሉ ለህክምና በሄደበት በአሜሪካ ከኢትዮጵያውያን ጋር ባደረገው ውይይት ከነረበት ግፊት የተነሳ ቅንጅቱ ገና ውሳኔ ሳይሰጥ 'ቅንጅት ፓርላማ አይገባም' ሲል ተናግሮ አደስ አበባ የነበረውን አመራር በጣም አበሳጭቶ ነበር፡፡" (ገፅ 505)

እንግዲህ እነዚህ ዶ/ር ብርሃኑ በተለሳለሰና በተድበሰበሰ ሁኔታም ቢሆን ስለኢንጂነር ኃይሉ በመፅሐፋቸው ውስጥ የሰጡአቸው አስተያየቶች -ኢንጂነር ኃይሉ ከፍተኛ የስብሰባ አመራር ችግር እንዳለባቸው፣ በጣም አኩራፊና ስሜታዊ ከመሆናቸውም የተነሳ ስብሰባ ረግጠው እስከመውጣት ድረስ እንደሚጋበዙ፣ የግልና የድርጅትን አቋም ለያይተው መግለፅ እንደማይችሉ፣ ከዚያም በላይ በቅንጅቱ ያልተወሰነን አቋም እንደተወሰነ አድርገው ዋሽተው የሚናገሩ እንደሆኑ በግልፅ አስቀምጠውታል፡፡ ይህ አይነት መሠረታዊ ድክመት ያለበትን ሰው ዶ/ር ብርሃኑ በምን መመዘኛ እንደገና የአመራርነት ብቃት አለው ብለው ለመከራከር እንደሚፈልጉ በእውነት ለእኔ አይገባኝም፡፡ ከዚህ አይነቱ የዶ/ር ብርሃኑ እርስ በርሱ የሚጋጭ አባባል የምረዳው ዶ/ር ብርሃኑ በአንድ በኩል ኢንጂነር ኃይሉን የአመራር ብቃት የላቸውም ብለው በግልፅ ለመናገር ድፍረት ያጡ መሆኑን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፈራ ተባ እያሉም ቢሆን በተዘዋዋሪ መንገድ የኢንጂነር ኃይሉን የመሪነት ብቃት ማነስ ለሕዝቡ ማጋለጥ የፈለጉ መሆናቸውን ነው፡፡ በእርግጥ እኔ እስከማውቀው ድረስ ዶ/ር ብርሃኑ ከመጀመሪያው ጀምሮ ኢንጂነር ኃይሉን ብቃት አላቸው ብለው እንደማያምኑ በሚገባ አውቃለሁ፡፡ ከቅንጅቱ ምስረታ ጀምሮ በግል ስንነጋገር ሁልጊዜ ያቀርቡት የነበረው

መከራከሪያ አቶ ኃይሉን ሊቀመንበር ካላደረግን በስተቀር መኢአድ ቅንጅቱ ውስጥ አባል ሆኖ ሊቀጥል አይችልም የሚል ነበር፡፡ በአጠቃላይ በቅንጅቱ የትግል ሂደት በተግባር እንደታየውም ሆነ ዶ/ር ብርሃኑ እራሳቸው በመፅሐፋቸው ባቀረቡት ምስክርነት ኢዴአፓ-መድህን ከመጀመሪያው ጀምሮ የኢንጂነር ኃይሉን ሊቀመንበርነት መቃወሙ ትክክል እንደነበርና በአንፃሩ እነ ዶ/ር ብርሃኑ የወሰዱት አቋም ምን ያህል የተሳሳተ እንደነበር አንባቢ በግልፅ የሚረዳው ይመስለኛል፡፡ በእርግጥ ኢዴአፓ-መድህን በዚያን ወቅት ኢንጂነር ኃይሉን በሚመለከት ያራመደው አቋም በማያጠራጥር ሁኔታ ትክክል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዶ/ር ብርሃኑን በደንብ ሳያውቃቸው የቅንጅቱ ሊቀመንበር እንዲሆኑ ጥቆማ ማቅረቡ ዛሬ ላይ ሆኜ ሳየው ስህተት እንደነበር ይሰማኛል፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ በቅንጅቱ ውስጥ 4ኛ ሰው ሆነው እያለ ምን ያህል ቅንጅቱን በሁሉም መስክ በበላይነት ለመቆጣጠር ያሳዩትን ስግብግብነት ከታዘብኩ በኋላ ሰውየው የቅንጅቱ ሊቀመንበር ሆነው ቢሆን ኖሮ ምን ያህል ገደብ ስተው የበለጠ አደጋ ውስጥ ይከቱን እንደነበር ሳስበው ይዘገንነኛል፡፡

## 2.2 በምርጫው ቅንጅት ስለሚያገኘው ከፍተኛ ውጤት የተሰጠ ቅድመ-ግምት፤

ቅንጅቱ ወደ ምርጫ ውድድር በገባበት ወቅት ከራሱ ድርጅታዊ ጥንካሬና ከወቅታዊው የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በዚያ ምርጫ የሚያገኘው ከፍተኛ ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል አስቀድሞ ለመገምገም መሞከሩ ተገቢ እርምጃ ነበር፡፡ በእርግጥ ቅንጅቱ በጉዳዩ ላይ ከመወያየት አልፎ ሊያገኘው በሚችለው ውጤት ላይ ከስሜታዊ አስተሳሰበ በፀዳ ተገቢ የሆነ የቅድመ-ትንበያ መደምደሚያ ላይ ደርሶ ቢሆን ኖሮ አሁን በቅንጅቱና በአጠቃላይም በትግሉ ላይ ደርሶ ያየነው አደጋ በብዙ መጠን ይቀንስ ነበር ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህ ውጤትን አስቀድሞ የመገምገም አጀንዳ ለቅንጅቱ የቀረበው በኢዴአፓ-መድህን ጉትጓችነት ሲሆን በአጀንዳው ዙሪያ የተፈጠሩት ሁለት የአመለካከት ልዩነቶችም የሚከተሉት ናቸው፡፡ በኢንጂነር ኃይሉ በኩል የቀረበው ቅድመ-ትንበያ በዘንድሮው ምርጫ የኢህአዴግን አፈናና ጫና ሁሉ ተቋቁመን ከ350 በላይ የሚሆን የፓርላማ መቀመጫ አሸንፈን የመንግሥትነት ስልጣን እንረከባለን የሚል ሲሆን - የኢዴአፓ-መድህንን ድርጅታዊ ግምገማ መነሻ አድርጌ እኔ ያቀረቡኩት ቅድመ-ትንበያ ደግሞ ምንም እንኳ ከኢህአደግ የተሻለ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ቢኖረንም በዘንድሮ ምርጫ ኢህአዴግ ሊፈፅም የሚችለውን አፈናና ጫና ተቋቁመን ልናገኘው የምንችለው ውጤት በፓርላማው ውስጥ በቂ የሚባል መቀመጫ ከማግኘትና አዲስ አበባ ከተማን ሙሉ በሙሉ ከማሸነፍ ያለፈ ሊሆን አይችልም የሚል ነበር፡፡ ኢንጂነር ኃይሉና እኔ ከላይ በተጠቀሰው ልዩነታችን ዙሪያ የውይይት መነሻ የሚሆን ወረቀት ለቅንጅቱ ምክር ቤት አቅርበን ውይይት ተደርጐበታል፡፡ በዚህ ውይይት ላይ  ኢንጂነር ኃይሉ የራሳቸውን አቋም የሚተነትን አንድ ገፅ ተኩል ጥቅል ይዘት ያለው ወረቀት ያቀረቡ ሲሆን በእኔ በኩል “ልናሸንፍ አንችልም” የምልበትን ምክኒያት በዝርዝር የሚተነትን 13 ገፅ ወረቀት አቅርቤአለሁ፡፡ ነገር ግን በአቀረብናቸው ወረቀቶች ይዘት ላይ ጥልቀት ያለው ውይይት ሳይካሄድ በቀረቡት ልዩነቶች ላይ ድምፅ እንድንሰጥ በመደረጉ፣ ጉዳዩ የነባራዊ ሁኔታ ትንታኔ መሆኑ ቀርቶ የፍላጐት ጉዳይ ብቻ ሆነና የኢንጂነር ኃይሉ አቋም በከፍተኛ ድምፅ አሸናፊ ሆኖ ተቀባይነት አገኘ፡፡

በዚህ ወቅት ዶ/ር ብርሃኑ እጃቸውን አውጥተው በማስቆጠር የእንጂነር ኃይሉን አቋም የደገፉ ሲሆን አሁን በፃፉት መፅሐፍ ላይም በተለባበሰ ሁኔታ የኢንጂነር ኃይሉ አቋም ደጋፊ እንደነበሩ አሳይተዋል፡፡ ነገር ግን ይኸ አጀንዳ ለውሣኔ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ዶ/ር ብርሃኑ የእኔን አቋም ይጋሩ እንደነበር በመፅሐፋቸው ውስጥ ሳይጠቅሱት አልፈዋል፡፡ በዚህ አጀንዳ ላይ የቅንጅቱ ምክር ቤት ውይይት ሲያደርግ በሁሉም አባላት መካከል ማለት ይቻላል በሁለት ጉዳዮች ላይ ምንም አይነት ልዩነት አልነበረም፡፡ ይኸውም ሁላችንም ቅንጅት ከኢህአዴግ የበለጠ ሕዝባዊ ተቀባይነት ያለው መሆኑንና የቅድመ-

ትንበያችን ውጤት ምንም ይሁን ምን የምርጫ ዘመቻውን ስናካሂድ “እናሸንፋለን” በሚል መንፈስ መሆን እንዳለበት ልዩነት አልነበረንም፡፡ መሠረታዊ ልዩነቶችን የሚመነጨው - አሁን ካለን ድርጅታዊ ጥንካሬ አንፃርና በአገራችን ካለው አጠቃላይ የፖለቲካ አሰላለፍ አንፃር ኢህአዴግ ሊያሳድርብን የሚችለውን አፈናና ጫና ተቋቁመን ምርጫውን ማሸነፍ እንችላለን ወይ? በሚለው ነጥብ ላይ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ቅንጅት በምርጫው ሂደት ውስጥ አልፎ ያገኘው ውጤት በሚገባ ስለታወቀ በቅድመ -ትንቢያው ወቅት የማንኛችን አቋም ትክክል ነበር የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ምንም የሚያከራክር ነገር ያለ አይመስለኝም፡፡ ምክኒያቱም የምርጫው ውጤት እራሱ ፍርዱን ሰጥቷል፡፡ ኢንጂነር ኃይሉ እንደገመቱት - የኢህአዴግን አፈናና ጫና ተቋቁመን ምርጫውን አሸንፈን መንግሥት አልሆንንም፡፡ ከኢህአደግ አፈናና ጫና ተርፎ ቅንጅቱ ያገኘው ውጤት በፓርላማ ውስጥ 109 ወንበርና በምክር ቤት ደረጀ አዲስ አበባ ከተማን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቀድሞውንም የኢዴአፓ-መድህን ትንበያ እንደነበር ግልፅ ነው፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ትክክልም ይሁኑም - አይሁኑም የኢንጂነር ኃይሉን አቋም መደገፍ መብታቸው ነው፡፡ ነገር ግን በመፅሐፋቸው ውስጥ አንድ ደብቀው ያለፉት ሃቅ አለ፡፡ ይኸውም -ይኸ አጀንዳ ለውይይት ቀርቦ ድምፅ እንዲሰጥበት እስከተደረገበት እለት ድረስ ዶ/ር ብርሃኑ ሙሉ በሙሉ የእኔ አቋም ደጋፊ ነበሩ፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን በግልፅ ለመፃፍ ካለመድፈራቸውም በላይ በአጀንዳው ላይ ድምፅ እንዲሰጥበት መደረጉን እንኳ ሳይገልፁ አድፈንፍነው አልፈውታል፡፡ ምክኒያቱም ትልቁ የቅንጅቱ ስህተት የመነጨው በዚህ አጀንዳ ላይ ከተወሰደው አቋም ስለሆነ ዶ/ር ብርሃኑ የዚህ ስህተት ተጋሪ መሆናቸውን በግልፅ ማመንና ለሕዝብ ማሳወቅ አልፈለጉም፡፡ ነገር ግን ዶ/ር ብርሃኑ ቀደም ሲል የኔን አቋም ይደግፉ እንደነበር በየአገኙት አጋጣሚ ዘንድሮ በዚህ ምርጫ አዲስ አበባን ነፃ ብናወጣና በፓርላማው 30% ያህል መቀመጫ ብናሸንፍ በሕይወታችን ትልቅ ታሪክ ሰራን ማለት ነው በማለት በግልፅ ይናገሩ ነበር፡፡ ለዚህም ነበር ከመጀመሪያው ዶ/ር ብርሃኑ ከፓርላማ ይልቅ ለአዲስ አበባ ምክር ቤት አባልነት መወዳደርን የመረጡት፡፡ እውነታው ይህ ባይሆንና ቀድሞውንም በአገር ደረጃ እናሸንፋለን የሚል እምነት ቢኖራቸው ኖሮ ዶ/ር ብርሃኑ በመፅሐፋቸው ላይ በግልፅ እንዳስቀመጡት ከአቶ በረከት ጋር ባደረጉት የውስኪ ውርርድ አዲስ አበባን እናሸንፋለን ሳይሆን በኢትዮጵያ ደረጃ እናሸንፋለን ብለው በተወራረዱ ነበር፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ማንም ሰው የሚመስለውን አቋም የመያዝ መብት አለው፡፡ ነገር ግን በዚህ የእናሸንፋለን አናሸንፍም ጥያቄ ዙሪያ አንድ ተራ የፓርቲ አባል ወይም ደጋፊ የቱንም ያህል የተሳሰተ ግምት ቢኖረው አይገርመኝም፡፡ በፓርቲ አመራር ደረጃ ያለን ሰዎች ግን በዚህ ጥያቄ ዙሪያ ይህን ያህል የሰፋ ልዩነት ይዘን መገኘታችን ለሰሚው ግራ የሚያጋባ ይመስለኛል፡፡ ምክኒያቱም ቢያንስ በሚከተሉት ጥቂት ምክኒያቶች ምን ያህል ያንን ምርጫ በአሸናፊነት መወጣት ለቅንጅቱ አስቸጋሪ እንደሆነ ለብዙዎቻችን ግልፅ ነበር፡፡ 1ኛ. በአገሪቱ ካሉ 547 የምርጫ ክልሎች ቅንጅት እጩዎች ማቅረብ የቻለው በ427 ክልሎች ብቻ ነው፡፡ ይህም ማለት ገና በምርጫው ሳንወዳደር በ120 የምርጫ ክልሎች አስቀድመን ተሸንፈናል ማለት ነው፡፡ 2ኛ. ከቅንጅት ይልቅ ለኢህአደግና ለአጋር ድርጅቶቹ የተሻለ ድጋፍ ሊኖራቸው በሚችለው በትግራይ፣ በአፋር፣ በሱማሌ፣ በሐረሬ፣ በጋምቤላና በቤንሻንጉል ክልሎች በርካታ መቀመጫዎችን ልናጣ እንደምንችል አስቀድሞ የታወቀ ነበር፡፡ 3ኛ. በኦሮሚያና በደቡብ ክልል ለረዥም ጊዜ ከኛ የተሻለ እንቅስቃሴ የነበራቸው ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ማለትም -ደቡብ ህብረት፣ ኦብኮና ኦፌዲን የመሳሰሉት ድርጅቶች ቢያንስ የተወሰኑ መቀመጫዎችን እንደሚሻሙን የሚያጠራጥር አልነበረም፡፡ 4ኛ. ኢህአዴግ በምርጫው ሊፈፅም የሚችለውን የአፈናና የማጭበርበር ድርጊት ሙሉ በሙሉ በታዛቢነት ለመከታተልና ለመቆጣጠር ከ90ሺ በላይ ታዛቢዎች ቅንጅቱ ያስፈልጉት ነበር፡፡ ነገር ግን ቅንጅቱ ማቅረብ የቻለው ከ15 ሺ ያልበለጡ ታዛቢዎችን ነበር፡፡ ስለዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ነባራዊ ሁኔታዎች ቅንጅቱ በምን አይነት ተዓምር ተወጥቶ እነ እንጂነር ኃይሉ ሻዎል እንደገመቱት ከ427 የምርጫ ክልሎች

ውስጥ 350 መቀመጫዎችን አሸንፎ መንግሥት ለመሆን እንደሚበቃ ለእኔ የፍላጐት ወይም የጥንቆላ ጉዳይ ከመሆን አልፎ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ግምት ሆኖ አልታየኝም፡፡ ሌሎቹን ምክኒያቶች ለጊዜው ወደጐን ትተን ቢያንስ በብዙ የምርጫ ጣቢያዎች የራሳችንን የምርጫ ታዛቢዎች ባላቀረብንበት ሁኔታ በዚያ መጠን ምርጫውን እናሸንፋለን ብሎ ለመገመት በቅድሚያ ኢህአዴግ ምንም አይነት የምርጫ ማጭበርበር የማይፈፅም ጨዋ ድርጅት ነው ብሎ ማመንን የሚጠይቅ ይመስለኛል፡፡

## 2.3. የምርጫ ችግሮችን የማጣራት ሂደት በተመለከተ የነበረን ልዩነት

ግንቦት 7/97ዓ.ም የምርጫው እለት ካለፈ በኋላ በምርጫው ዙሪያ የተፈጠረውን ችግር እንዴት እንፍታው? የሚለው ጥያቄ በቅንጅቱ ውስጥ መሠረታዊ የልዩነት ምንጭ ነበር፡፡ በዚህ ጥያቄ ዙሪያ ዶ/ር ብርሃኑ ያራመዱት አቋም ችግሩ መፈታት ያለበት በምርጫ ቦርድ አማካኝነት በሚካሄድ የማጣራት ሂደት ነው፡፡ በምርጫ ቦርድ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለንም ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ይዘን መሄድ ይገባናል፡፡ ይህንን ስናደርግም የዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ ድጋፍ ለኛ ይሆናል፡፡ ከዚህ ውጭ በሌላ መንገድ ችግሩ ሊፈታ አይችልም የሚል ነበር፡፡ ከዚህ በተለየ እኔ ያራመድኩት አቋም ደግሞ- "ችግሩን ለመፍታት የሚደረገው ዲፕሎማሲያዊ ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ -ችግሩ በምርጫ ቦርድና በፍርድ ቤት አማካኝነት መፍትሄ ያገኛል ብሎ መገመት የዋህነት ነው፡፡ እነዚህ በገዥው ፓርቲ ቁጥጥር ስር ያሉ ተቋማት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ችግሩን ይፈቱታል ብለን ግዴታ ውስጥ ከገባንና ስምምነት ከተፈራረምን በመጨረሻ እራሳችንንም ሆነ የተፈጠረውን ችግር መውጫ ወደሌለው አጣብቂኝ ውስጥ እንከታለን፡፡ እነዚህ ተቋማት የሚያካሂዱት የማጣራት ሂደት ገዥውን ፓርቲ እንጂ እኛን ሊጠቅም እንደማይችልና የነዚህን ተቋማት ውሳኔም መጨረሻ ላይ አሜን ብለን ለመቀበል እንደማንችል አስቀድመን እያወቅን ወደዚህ አይነት ስምምነት ውስጥ መግባት የተፈጠረውን ችግር የበለጠ ከማወሳሰብ አልፎ መፍትሔ ሊያመጣ አይችልም፡፡ እንዲህ አይነቱ ሂደት ኢህአዴግ እራሳችን ወደን የገባነውን ስምምነት መሠረት አድርጐ እኛን የህግ አጣብቂኝ ውስጥ ለማስገባትና በምርጫው ወድቀውበት የነበሩ አንዳንድ ባለሥልጣናቱና እንደገና እንዲያሸንፉ ለማድረግ ይጠቅመዋል እንጂ ለእኛ የሚፈይደው ነገር የለም፡፡ ስለዚህ የሚሻለው አማራጭ ከዲፕሎማሲያዊው ጥረት በተጨማሪ ጉዳዩን የጉዳዩ ባለቤት ወደ ሆነው ወደ ሕዝቡ በመውሰድ ሕዝቡ በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ ተቃውሞውን የሚያሰማበትን መድረክ ማዘጋጀትና የተፈጠረው ችግር ወደባሰ ውስብስብ ሁኔታ ከመግባቱ በፊት ፖለቲካዊ መፍትሄ አግኝቶ በአጭር ጊዜ መቋጨት ይገባዋል የሚል ነበር፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በእኔ በኩል ይቀርብ የነበረው ሌላው አቋም- በዚህ አይነት የተንዛዛና በመጨረሻም አስተማማኝ መፍትሔ በማያመጣ ሂደት ውስጥ ከገባን በቅንጅቱና በሕዝቡ መካከል የአጀንዳ ልዩነት እየተፈጠረ ይመጣና እኛ እንደ ድርጅት ልንቆጣጠረውና ልንመራው የማንችል ደም መፋሰስ የሚያስከትል አገራዊ ቀውስ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ስለዚህ ሕዝቡ ወደዚህ አይነቱ አደገኛ የተናጠል እርምጃ ከመገፋቱ በፊት የተጠኑ ህጋዊና ሰላማዊ የትግል ስልቶችን በመንደፍ ትግሉን የመምራቱን ሚና ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራችን ስር ማዋል አለብን የሚል ነበር፡፡ በእነዚህ ሁለት ልዩነቶች ዙሪያ ቅንጅቱ አንድ ግልፅ አቋም መውሰድ ተስኖት ሲውተረተር የሕዝቡን ሰላማዊ ትግል በአግባቡ ተቆጣጥሮ መምራት ባለመቻሉ በተፈጠረው ክፍተት ሕዝቡ በሌሎች ኃይሎች ኃላፊነት የጐደለው ሴራ ተገፋፍቶ ወደ ሰኔ 1/97ዓ.ምቱ አሳዛኝ ክስተት ውስጥ ሊገባ ቻለ፡፡ ከዚያም በኋላ የምርጫውን የማጣራት ሂደት የተቃወምኩት እኔ ከቅንጅቱ አመራር ተነጥዬ በእገታ ውስጥ እንድቀመጥ ከተደረገ በኋላ በዋናነት በዶ/ር ብርሃኑ ተዋናይነት ኢህአዴግ በፈለገው ሁኔታ ሙሉ በሙሉ የማጣራቱ ሂደት ስምምነት እንዲፈረም ተደረገ፡፡ ማለትም - የማጣራት ሂደት የሚካሄድባቸው ቦታዎች የትኞቹ እንደሚሆኑ አስቀድሞ የሚወስነው ምርጫ ቦርድ

እንዲሆን ፤ በማጣራቱ ሂደትም ልዩነት ሲፈጠር ውሳኔ የሚሰጠው በሦስት አካላት ድምፅ ሰጭነት እንዲሆንና በዚህም የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ቅንጅት፣ ኢህአዴግና ምርጫ ቦርድ እኩል አንድ አንድ ድምፅ እንዲኖራቸው (ማለትም ኢህአዴግና ምርጫ ቦርድ የደገፉት ሃሣብ ተቀባይነት ያገኛል)፤ በዚህ የማጣራት ሂደት ቅሬታ አለኝ ብሎ የሚያምን ድርጅትም ቅሬታውን ወደፍርድ ቤት እንጂ ወደሌላ የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዳይወስድ፤ ፍርድ ቤት በመጨረሻ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻና ይግባኝ የሌለው እንዲሆን ቅንጅቱ ተስማምቶ ፈረመ፡፡ ይህ ስምምነት በተፈረመበት ወቅትም ይህ ስምምነት ተፈፃሚ እንዲሆን ቅንጅቱ በቅድመ ሁኔታነት አቅርቦት የነበረውን ሃሣብ ዶ/ር ብርሃኑ ያለ ቅንጅቱ አመራር ፈቃድ ምርጫ ቦርድ ድረስ ሄደው ቅድመ ሁኔታው እንዲነሳ ተስማምተው በመፈረማቸው ምክኒያት ስምምነቱ ወደ ተግባር እንዲለወጥ ተደረገ፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ በዚህ የማጣራት ሂደት ስለነበራቸው ሚና በመፅሐፋቸው ውስጥ አለባብሶ የማለፍ ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም ይህ ስምምነት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በዚህ መልክ እንዲፈረም በማድረግም ሆነ የማጣራቱ ሂደት በተግባር ከተጀመረም በኋላ ሂደቱ ሳይቋረጥ እስከ ፍርድ ቤት ድረስ ሄዶ ኢህአደግ በፈለገው መልኩ ሙሉ በሙሉ እንዲቋጭ በማድረግ ረገድ ዋናውን ሚና የተጫወቱት እሳቸው ነበሩ፡፡

ይህ በዋናነት ዶ/ር ብርሃኑ ያራመዱት አቋም ምን ያህል ቅንጅቱን እንደጐዳውና በመጨረሻም የማይወጣበት አጣብቂኝ ውስጥ እንዳስገባው ለማንኛውም የፖለቲካ ሀሁን ለሚረዳ ሰው ግልፅ ይመስለኛል፡፡ ቅንጅት አስቀድሞ በገባው ስምምነት መሠረት የማጣራቱ ሂደት እስከ ፍርድ ቤት ድረስ ሄዶ ከተጠናቀቀ በኋላ የማጣራቱን ሂደት ውጤት አልቀበልም ማለት ህገ-ወጥነት እንዲሆን አድርጐ ኢህአዴግ ቅንጅትን ለመክሰስና አጣብቂኝ ውስጥ ለማስገባት እንዴት እንደቻለ በግልፅ አይተናል፡፡ እንዲህ አይነት ህጋዊ ድጋፍ ከማግኘትም በተጨማሪ ኢህአዴግ ቀደም ሲል በምርጫው የተሸነፋበትን ባለሥልጣናት እንደገና ለማስመረጥ ሂደቱን እንዴት እንደተጠቀመበትም በግልፅ አይተናል፡፡ በመጨረሻም የቅንጅቱ፣ የሕዝቡ፣ የዲፕሎማቲክ ኮሚኒቲውና የገዥው ፓርቲ አጀንዳዎችና ፍላጐቶች በተለያየ አቅጣጫዎች ተጉዘው የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ሂደት እንዴት እንደገና 15 ዓመታት ወደኋላ እንደተመለሰ አይተናል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ አጀንዳ ዙሪያ ዶ/ር ብርሃኑ ያራመዱት አቋም ምን ያህል ጐጂና ከንቱ እንደነበረ አምነው ለመቀበል ያልደፈሩ ቢሆንም እራሳቸው ዶ/ር በርሃኑ በመፅሐፋቸው ውስጥ ስለማጣራቱ ሂደት የገለፁትን አንድ አረፍተ ነገር ጠቅሶ ማለፉ ቀድሞውንም የማን አቋም ትክክል እንደነበር ለማሳየት በቂ ማረጋገጫ ይመስለኛል፡፡

“… የማጣራት ሂደቱ በዚህ መልክ ከተጠናቀቀ በኋላ ራሳችንን ያገኘነው ከማጣራቱ ሂደት በፊት የነበርንበት ሁኔታ ላይ ነው፡፡” (ገፅ 418)

ዶ/ር ብርሃኑ ያዋጣል ብለው ያራመዱት አቋም ምን ያህል ከንቱ እንደነበር በዚህ መልኩ እራሳቸው ያረጋገጡት ቢሆንም እሳቸው እንዳሉት ግን ቅንጅቱ በዛን ወቅት ይገኝ የነበረው ከማጣራቱ ሂደት በፊት የነበረበት ሁኔታ ላይ አልነበረም፡፡ በፖለቲካ፣ በዲፕሎማሲም ሆነ በህግ አግባብ ቅንጅቱ ከማጣራቱ ሂደት መጠናቀቅ በኋላ በከፍተኛ ደረጃ ደካማ አቋም ላይ እንዲገኝ ነበር የተደረገው፡፡

## 2.4 <u>የጊዜያዊ የሽግግር /ጥምር/መንግሥት ጥያቄ</u>

ይህ በዶ/ር ብርሃኑ መሪ ተዋናኝነት በቅንጅቱ ስም ለመንግሥት ቀርቦ የነበረው የጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት ጥያቄ የአንድ ሳምንት ጋዜጦች ማሻሻጫና የኢህአዴግ መሳቂያና መሳለቂያ ከመሆን አልፎ ለወቅቱ የፖለቲካ ችግር ምንም የፈየደው ነገር እንደሌለ በተግባር ታይቷል፡፡ ጥያቄው ከመንግሥትም ሆነ ከአለም አቀፉ ህብረተሰብ

ተገቢ መልስና ትኩረት ያላገኘ ከመሆኑም በላይ የጥያቄው ፖለቲካዊ ትርጉም ምን ማለት እንደሆነ እንኳ የቅንጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ጭምር በውል አልተረዱትም ነበር፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ጥያቄው የህብረቱ እንጂ የቅንጅቱ አይደለም፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ አንድም ቀን የቅንጅቱ አመራር ተወያይቶ አያውቅም፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ በቅንጅቱ ስም ለመንግስት ስለመቅረቡ ኢንጂነር ኃይሉ ሻዎልን ጨምሮ ሌሎች የቅንጅቱ አመራሮችና አባላት የሰሙት ዜናው በግል ጋዜጦች ላይ ሲወጣ ነው፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሊያነጋግሯቸው እንደሚፈልጉ በስልክ ሲነገራቸው ይህንን በግላቸው ያረቀቁትን ሰነድ ወስደው ሰጧቸው እንጂ - እንዲህ አይነት ሰነድ ለመንግሥት እንዲቀርብ በቅንጅቱ አልተወሰነም፡፡ አይደለም ቀርቶ የሰነዱ መቅረብና የዶ/ር ብርሃኑ ቅንጅቱን ወክሎ ከጠ/ሚኒስትሩ ጋር  መገናኘትም በወቅቱ በቅንጅቱ የሚታወቅና የተወሰነ አልነበረም፡፡ ይህ እውነት ስለመሆኑም ዶ/ር ብርሃኑ በመፅሐፋቸው ላይ ጠ/ሚኒስትሩን ለማነጋገር እንደሚሄዱ ቅንጅቱ ፅ/ቤት ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች በስልክ ደውለው ከመናገራቸው በስተቀር ድርጅታዊ ውክልና ተሰጥቷቸው እንዳልሄዱ ገልፀውታል፡፡

ጉዳዩ በቅንጅቱ ያልተወሰነ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በቅንጅቱ ተወስኖ ቀርቦም ቢሆን ኖሮ ምንም አይነት የፖለቲካ ፋይዳ የሚያስገኝ ጥያቄ አልነበረም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ እንዲህ አይነቱ ጥያቄ የህግ ጥያቄ ያስነሳል፡፡ በአሁኑ ወቅት አገሪቱ እየተገዛችበት በምትገኘው ህገ-መንግሥት፣ መንግሥት እንዴትና በማን መቋቋም እንዳለበት ከተደነገገው የህግ አግባብ አንፃር የሽግግር መንግሥት ጥያቄ ምንም አይነት ህጋዊ መሠረት የለውም፡፡ ሁለተኛ - አንድ የፖለቲካ ድርጅት በምርጫ ውድድር ውስጥ እራሱን ካስገባ በኋላ የሕዝቡ ትክክለኛ ድምፅ እንዲከበር ትግል ከማድረግ አልፎ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከሕዝብ ውሳኔ በተቃራኒ እራሳቸው ተስማምተው የተለየ አይነት በሕዝብ ያልተመረጠ መንግሥት እንዲያቋቁሙ መጠየቅ ህጋዊ ካለመሆኑ በላይ ፖለቲካዊ ትክክለኛነት የለውም፡፡ ሦስተኛ - ይህ በዶ/ር ብርሃኑ ተረቆ የቀረበው ሰነድ የሚቋቋመው የሽግግር መንግሥት በምርጫው በተገኘው የምርጫ /ምርጫ ቦርድ በተቀበለው/ ውጤት መሠረት ፓርላማ እንዲቋቋምና ፓርቲዎች ፓርላማ ውስጥ በሚኖራቸው የወንበር ድርሻ መሠረትም የሚኒስትርነት ቦታ እንዲሰጣቸው የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህ አይነቱ ጥያቄ የወቅቱን የሕዝብ ድምፅ የማስከበር የቅንጅት ጥያቄ በአንድ ጊዜ ወደ ሥልጣን ክፍፍል ጥያቄነት የሚያወርድ ከመሆኑም በላይ ጥያቄው በመንግሥት ተቀባይነት አግኝቶ ቢሆን እንኳ ኖሮ ለቅንጅቱ ፖለቲካዊ ኪሳራ እንጂ ትርፍ የሚያስገኝ አልነበረም፡፡ ምክኒያቱም በሚመሠረተው የኢህአዴግ መንግሥት ውስጥ ጥቂት የቅንጅት ሰዎች የሚኒስትርነት ሹመት ማግኘታቸው የጥቂት ግለሰቦችን የሥልጣን ፍላጐት ከማርካት አልፎ ለወቅቱ የፖለቲካ ችግር የሚያበረክተው የተለየ አስተዋፅኦ አይኖርም ነበር፡፡

ከሁሉም በላይ ግን እንዲህ አይነቱ ትርጉም የለሽ እንደሆነ አስቀድሞ የታወቀ ጥያቄ በቅንጅት ስም መቅረቡ የሚያሳየን ቅንጅቱ በዚያን ወቅት ግለሰቦች ያነሱትን ሃሣብ ሁሉ እያንጠለጠለ ከቦታ ቦታ የሚዘል እንጂ እንደ አንድ የሚሰራውን የሚያውቅ የፖለቲካ ድርጅት የተጠናና የተመከረበት አቋም ይዞ የሚሰራ አለመሆኑን ነው፡፡ እውነታው ይህ ባይሆን ኖሮ - በመጀመሪያ በምርጫ ቦርድ በኩል የሚደረገውን የማጣራት ሂደት እንደ መጨረሻ ውሳኔ እቀበላለሁ ብሎ ከፈረመ በኋላ እንደገና በዚህ መንገድ የሄደበት መንገድ ስህተት መሆኑን ሲገነዘብ ህጋዊና ፖለቲካዊ መሠረት የሌለው የሽግግር መንግሥት ጥያቄ ባላቀረበ ነበር፡፡ ከዚያም በኋላ ይህ የሽግግር መንግሥት ጥያቄ የትም የማያደርስ መሆኑን ሲገነዘብ እንደገና ስምንቱ ቅድመ ሁኔታዎች ከተመለሱልኝ የምርጫውን ውጤት ተቀብዬ ፓርላማ እገባለሁ ወደሚለው ሌላ ጥያቄ ባልተሸጋገረ ነበር፡፡ ኢዴአፓ-መድህን ይህንን የሽግግር መንግሥት ጥያቄ ትርጉም የለሽነት በውል ተገንዝቦ የተቃወመው የቅንጅቱ አባል ከመሆኑ በፊት የህብረቱ አባል በነበረበት ወቅት ነው፡፡ ኢዴአፓ-መድህንና መኢአድ ከህብረቱ እንዲወጡ ያስገደዳቸው አንዱ ምክንኒያትም ይህ የማያዛልቅ የሽግግር

መንግሥት ጥያቄ ነበር፡፡ ይህ ጥያቄ በቅንጅት ስም ለመንግሥት በቀረበበት ወቅትም ኢ.ዴ.አ.ፓ- መድህን እንዲህ አይነቱን ጥያቄ እንደማይጋራ ለቅንጅቱ በግልፅ ያሳወቀ ከመሆኑም በላይ ጥያቄው በማንና እንዴት እንደቀረበ ማብራሪያ እንዲሰጠው ለቅንጅቱ በደብዳቤ ጠይቆ ጥያቄው በዶ/ር ብርሃኑ በኩል በግል የቀረበ እንጂ ቅንጅቱ በወቅቱ በነበረው የአሰራር ደንብ መሠረት ውሣኔ ያልተሰጠበት ስለመሆኑ በኢንጂነር ኃይሉ በኩል ተገልፆለታል፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ግን ይህንን እውነታ በመደበቅ ቅሬታ የተነሳው በእኔ በልደቱ በግለሰብ ደረጃ እንደሆነ አድርገው በሰፊው አትተዋል፡፡ ነገር ግን አዲስ ፖለቲከኛ በመሆናቸው ምክኒያት የቅንጅቱ አባል ፓርቲዎች ቀደም ሲል በተለያዩ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ዙሪያ የየራሳቸው አቋም እንደነበራቸው መገንዘብ ያልቻሉት ዶ/ር ብርሃኑ ተኝተው ሲነሱ ብልጭ ያለላቸውን ሃሣብ ሁሉ እየያዙ ወደ አምባሳደሮችና ወደ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ባለስልጣናት መሮጥን የየእለት ስራቸው አድርገው ይዘውት ነበር፡፡ ለዛሬው በዚሁ ላብቃና የበለጠ በስፋት መታየት ባለባቸው ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ማለትም ፓርላማ በመግባትና ባለመግባት ጥያቄና በቅንጅቱ የውህደት ጉዳይ ላይ ስለነበረው ልዩነት በሚቀጥለው ሣምንት እመለስበታለሁ፡፡

ይቀጥላል….